# ተከተል ፈለጉን

## የኔሰው ገብሬን

ከቀመሩ ደሳለኝ

እዉነትም የነሰው

የወቅቱ ጀግናው

የአገርን ጥፋት ማየት የማይወደው

ለህገ-ወጥ ህግ አልገዛም ያለው

ለነፃነት ፋና ቀዲሞ የምተው

ለሰዎች ደህንነት ራሱን የሰጠዉ

ለአገር ቅዲሚያ ፍቅርን ህይወቱን ከፈለው

ወራሪው ወያኔ ብዙ አስመርሮት ነው

ጋዙን አርከፍክፎ የተቀጣጠለው

እጂጉን ጭቆና ግፉ ብዝቶበት ነው

እኔ ላንተ ብሎ መሰዋዕት የሆነው።

የዋካው መምህር ያ ጠመኔ ትጥቁ

እንደ ጧፍ ነደደ ለዕውነት ለሀቁ

የጥበብ መምህር ዘርን የሚዘራ

ቀለጠ እንደ ሻማ ብርሀኑን ሊያበራ

መምህሩ አባቴ የጥበቡ ጌታ

አንተ ጋይተህ ነደህ ሆንክልኝ አለኝታ

ሻማ ሆኖ ነዶአል የመምህር ሥራ

እኔም ተከትዬ ብርሀኑን ላበራ

የነፃነት ዕጦት በደል ሰለቸኝ

ጠመኔ መታጠቅ ጠበንጃ ሆነኝ።

እኔ ካንተ በፊት ለነፃነት ብሏል

ቁጩ የመረረው ለወገኑ ሆኗል

ከኔ ተማር ብሎ እሱ እሳት አንዷል

በፍጹም በፅናት ፍቅሩን አሳይቷል

ነፃነት ዋጋ አለው ተከተለኝብሏል

ከእንግዲህ ያንተነው ጀግና ሰው የመምሰል

ወንድነት ይኑርህ ፈለጉን ተከተል።

**የጀግኖች አገር ኢትዮጵያ**

**ለዘለዓለም ትኑር**

**11-18-2011**